# አሁንም ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ እንዲሆን እንፈልጋለን!!

**ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)**

**የተሰጠ መግለጫ**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በምክክር ደረጃ ከተቋቋመ ጀምሮ ካነሳቸው አንገብጋቢ ፖለቲካዊ ጉዳዮች አንዱ መጪው ምርጫ ነፃ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸትን የተመለከተ ነበር። ለዚህ ሲባልም ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ ሊያደርጉት ይችላሉ ያላቸውን አሳሳቢ ጉዳዮች ለይቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ይህን አጀንዳውን ለዲፕሎማቲኩ ማህበረሰቡ ጭምር በማሳወቅ ገንቢ ሚናቸውን እንዲያበረክቱ ሲያሳስብ በተለይ የኢትዮጵያ አጋር ቡድን (Ethiopian Partners Group) ከተባለው የበርካታ አገሮች ዲፕሎማቶች ስብስብ ጋር በዚህ አጀንዳ ዙሪያ ተደጋጋሚ ውይይቶችን አካሂዷል። በመሆኑም በሰኔ 2001 ዓ.ም ይህን ቡድን በመወከል የእንግሊዝ ኤምባሲ ሰዎች ከመድረኩ ተወካዮች ጋር ተገናኝተው ኢህአዴግ በምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ጉዳይ ከተቃዋሚዎች ጋር ለመነጋገር እንደሚፈልግ ገልፀዋል። የመድረኩ ተወካዮች በወቅቱ ለአገናኙ ምላሽ ሲሰጡ በምርጫው ሥነ-ምግባር ደንብ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ ሊያደርጉ በሚችሉ ወሳኝ ጉዳዮች ጭምር ለመደራደር እንደሚፈለጉ አስታውቀዋል። ለዚህም ኢህአዴግ ዝግጁ ከሆነ እንዲያሳውቃቸው ጥያቄ አቅርበዋል።

ከቀናት በኋላ ኢህአዴግ መጀመሪያ በፖርላማ መቀመጫ ላላቸው የመድረኩ አባል ድርጅቶች፣ ኋላ ላይ ደግሞ ለስምንቱ የመድረክ አባል ድርጅቶች በምርጫ ሥነ-ምግባርና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ መደራደር እንደሚያስፈልግ ደብዳቤ ጽፏል። መድረኩም ይህን የኢህአዴግ የግብዣ ደብዳቤ መሠረት በማደረግ በውስጡ ሠፊ ውይይት አካሂዷል። በወቅቱም መድረክ ጅምሩ አበረታች መሆኑን ተቀብሎ በመነጋገሪያ አጀንዳዎችና በድርድሩ አካሄድ ግን ኢህአዴግ ካቀረበው የተለየ አማራጭ እንደሚያስፈልግ ተስማምቷል።

መድረክ ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ ይሆን ዘንድ የሥነ-ምግባሩ ደንብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አንገብጋቢ ናቸው ያላቸው የአገራችን ተጨባጭ ፖለቲካዊ እውነታዎችን መሠረት ያደረጉ አጀንዳዎች ለድርድር እንዲቀርቡ ኢህአዴግን ጠይቋል። ከነዚህ መድረኩ ካቀረባቸው የድርድር ነጥቦች መካከል:-

1ኛ በሕገ-መንግሥቱ የተደነገጉ በነፃ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብቶች በሁሉም ወገኖች የሚከበሩበት፤ በፖለቲካ አባልነት መነሻነት የሚከሰቱት አድሎዎች የሚቀሩበትና የሕግ የበላይነት የሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዲኖር በዚህ መሠረትም ከፖለቲካ ጋር በተገናኙ ሁኔታዎች በማሳበብ ከሕግ አግባብ ውጭ የታሰሩት በርካታ ዜጎች የሚፈቱበት፤ እንዲሁም ከለጋሽ ሀገሮችና ድርጅቶች የሚገኘውና ከመንግሥት የሚመደበው የረሀብ ርዳታ፤ የድህነት ማስወገጃና የሥራ ፈጠራ መርሀ-ግብሮች ማስፈፀሚያ ድጋፎች ከፖለቲካ አባልነትና ደጋፊነት ጋር ሳይያያዙ በፍትሐዊነት ለተጠቃሚው ህዝብ እንዲያደርሱ ያለመደረጉ በምርጫ ሂደት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ በመሆኑ የሚቀርበት ሁኔታ እንዲፈጠር፤

2ኛ/ የምርጫ ሥርዓቱን ነፃና ፍትሓዊ ለማድረግ የምርጫ አስፈፃሚውን አካላት የመመልመልና የማሰማራት ተግባራት ግልጽና ፓርቲዎችን አሳታፊ ስለሚሆንበትና የምርጫ አፈፃፀም ሥነ-ምግባር ደንብ ስለሚቀረጽበት የምርጫ ሥርዓትን በበላይነት የሚቃኝ (ሞኒተር የሚያደርግ) ነፃ አካል ስለሚቋቋምበት የህዝብ ታዛቢዎች በሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ተሳትፎ በህዝቡ ስለሚመረጡበት፤ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ገለልተኛ ታዛቢዎች ስለሚሰማሩበትና ምርጫን የመታዘብ ሥነ-ምግባር ደንብ ስለሚቀረጽበትና እንዲሁም የመንግሥት ተቀጣሪዎች (ሠራተኞች) እና የህዝብ ሀብትና ንብረት ለፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ እንዳይውሉ ስለሚደረግበት፤ ለምርጫው ውዝግቦች አፋጣኝ ዳኝነት የሚሰጡ ልዩ የምርጫ ጉዳዮች ችሎቶች ስለሚቋቋሙበት፤ ሁኔታ ግልጽ ወይይት እንዲደረግና የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደረስ።

3ኛ/ ሕገ-መንግሥቱ «ለፕሬስ ልዩ ጥበቃ ይደረጋል»፤ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ለሁሉም በእኩል ያገግላሉ በሚለው መሠረት የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት የሚከበርበትና የፖለቲካ ፓርቲዎች የሕዝብ (የመንግሥት) መገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ፍትሓዊነት የሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዲኖር የሚሉ ይገኙባቸዋል።

መድረክ በአገራችን ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ይካሄድ ዘንድ እነዚህንና ሌሎች ጉዳዮችን ከሥነምግባር ደንቡ ጋር በማያያዝ ሳይሆን ራሳቸውን ችለው በጥልቀት ድርድር እንዲደረግባቸው ሲያቀርብ አሁን በአገራችን ያለውን እጅግ የጠበበ ፖለቲካዊ ስነ ምህዳር" መሰረት በማድረግ" ኢህአደግ ከመድረክ አባል ድርጅቶችና በደጋፊዎቻቸው ላይ እያደረሰ ለአለው ከፍተኛ ጫናና ወከባ ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ መፍትሔ

እንዲያበጅላቸው ካለው ጽኑ አቋም በመነሳት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ መድረክ አባላቱና ደጋፊዎቹ በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ሁሉ እስር፣ እንግልት፣ ማስፈራራትና ጥቃት በስፋት እየተፈፀሙባቸው በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እንዲደራደርባቸው ይፈልጋል፡፡ ከዚህ ሌላም የህዝብ ስብሰባና ቅስቀሳ ማካሄድ እጅግ አስቸጋሪ የሆበት፣ ጽ/ቤቶች የተዘጉበት፣ የተከፈቱት ጽ/ቤቶችም እየተጠቁና እየተዘረፉ መስራት ያልቻሉበት ሁኔታም በስፋት እየታየ ይገኛል፡፡ ይህንንም ክስተት በመደራደሪያ አጀንዳነት አቅርቦ ከገዢው ፓርቲ ጋር ሊነጋገርበት ይፈልጋል፡፡

መድረክ የምርጫ አስፈፃሚዎችና የምርጫ ታዛቢዎች ገለልተኛ አለመሆን በምርጫው ፍትሓዊነትና ነፃነት ላይ ሊያሳድር የሚችለውንም ተጽእኖ ከወዲሁ አጢኖታል፡፡በመሆኑም ከኢህአዴግ ጋር በጥልቀት እንዲወያይበት ያቀረበው አንዱ ወሳኝ ጉዳይ ሆኗል፡፡

በምርጫው ፍትሓዊነትና ነፃነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል ብሎ ያመነበት ሌላው ጉዳይ ደግሞ የግሉ ሚዲያ ነፃነትንና የመንግሥት ሚዲያ ፍትሓዊነትን የተመለከተ ነው፡፡ የግሉ ሚዲያ ሥርዓት ባለው መንገድ በነፃነት የሚሠራበትና አሁን ገዢው ፓርቲ በብቸኝነት ለፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ በስፋት እየተጠቀመበት ያለው የመንግሥት ሚዲያ ሁሉም ፓርቲዎች በፍትሐዊነት የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ መድረኩ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው የድርድር አጀንዳ ነው፡፡

ስምንቱ የመድረክ አባል ድርጅቶች ከፍ ብለው የተገለፁትንና ሌሎች ወሳኝ ጉዳዮችን በማቅረብ ከኢህአዴግ ጋር የሁለትዮሽ ድርድር ለማድረግ ቢጠይቁም ኢህአዴግ አዎንታዊ መልስ አልሰጠም፡፡ በመሆኑም ራሱ ከቀረፀው አጀንዳና የድርድር አካሄድ ብቻ እንጂ ሌላ አማራጭ ለመቀበል ፍቃደኛ ባለመሆኑ ከኢህአዴግ ጋር መስማማት አልተቻለም፡፡

መድረክ በተደጋጋሚ ከኢህአዴግ ጋር የሚያደርገው ድርድር ውጤታማ ይሆን ዘንድ በተናጠል ያቀረብናቸው የድርድር ነጥቦችን በሁለትዮሽ ውይይት የሥነ-ምግባር ደንቡን ደግሞ ኢህአዴግ ከጋበዛቸው ሌሎች ድርጅቶች በጋራ ለመደራደር ፈቃደኝነቱን ቢገልጽም ኢህአዴግ መጀመሪያ ካቀረበው አጀንዳና የድርድር አግባብ ውጭ ሌላ አግባብ ለመቀበል እንዳልተዘጋጀ በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡ መድረኩ አሁንም በአገራችን ባሉት

አንገብጋቢ ፖለቲካዊ ጉዳዩች የሁለትዮሽ ድርድር ማድረግ የዴሞክራሲ ሂደቱን ያጠናክራል፣ ምርጫውንም ነፃና ፍትሓዊ መሠረት እንዲኖረው ያስችላል ብሎ ያምናል:: በመሆኑም ባነሳናቸው ጉዳዮች ተመሳሳይ ግንዛቤ ከሌላቸውና በባለቤትነት ከማይቆሙላቸው ፓርቲዎች ጋር አብሮ በመደራደር ጊዜውን ለማጥፋት አልፈለገም:: ድርድሩ የችግሩ ምንጭ ከሆነው ከኢህአዴግ ጋር እንዲሆን መፈለጉም በቂና አሳማኝ ምክንያት አለው::

ኢህአዴግ ለድርድር ከጋበዛቸው ፓርቲዎች ለአንዳንዶቹ በአገራችን ያለው ፖለቲካዊ ምህዳር ያልጠበበ ስለ መሆኑ፣ ታማኝ ተቃዋሚዎች በመሆናቸው፣ የትግላቸው አቅጣጫ በተቃዋሚዎች ላይ ያነጣጠረ በመሆኑና የተቃዋሚ ተቃዋሚ ሆነው ለመቆም በመወሰናቸው ከእነሱ ጋር መደራደር ትርጉም እንደሌለው የመድረኩ አባል ፓርቲዎች እምነት በመሆኑ የችግሩ ሰለባዎች የሆንነው ከችግሩ ፈጣሪ ጋር ብቻ ለመደራደር መምረጣችን በመርህም ሆነ በአካሄድ ትክክል እንደሆነ አሁንም እናምናለን:: በመሆኑም መድረኩን በሚያሳስቡት ጉዳዮች ዙሪያ የሁለትዮሽ ድርድር ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን አሁንም ቢሆን ለማረጋገጥ እንወዳለን::

ኢህአዴግ ያቀረብንለትን የመደራደሪያ አጀንዳ ወደ ጎን በመተው ራሱ ያቀረበውን ጥሪ ከተቀበሉትና በቀረፀው አጀንዳና አካሄድ ለመነጋገር ከተስማሙ ፓርቲዎች ጋር ባለፈው ሳምንት በታላቅ ፌስታ የስምምነት ፊርማ ሥነ-ሥርዓት አካሂዷል:: በዚህ ሥነ-ሥርዓት ወቅት መድረኩን ያሳሰበው ሁኔታ ሲከሰቱ ተስተውሏል:: ይኸውም አራቱን ፓርቲዎች ወክሎ የመክፈቻ ንግግር ያደረገው የኢህአዴግ የፖርላማ ተጠሪና ተደራዳሪ መድረኩ ኢህአዴግ ባዘጋጀው አጀንዳና አካሄድ ባለመስማማቱና ብቻ ባለመደራደሩ ሠላምን እንደማይፈልግ አድርጎ ትችና ወቀሳ ማቅረቡ ነበር::

በኛ እምነት የሁከት ምንጭ እየሆነ ያለው ኢህአዴግ ራሱ ነው:: መግባባት፣ ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር ምክንያት እየሆነ ያለው ኢህአዴግ ራሱ ነው:: በዜጎች መብት ላይ ከፍተኛ የአፈናና የወከባ በደል እየፈፀመና ዋነኛ የሁከት ምንጭ ነው እየሆነ ያለው ኢህአዴግ ራሱ:: ይህን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል የፖሊስ፣ የመከላከያ፣ የደህንነት ተቋማትን የተቆጣጠረውም ኢህአዴግ ራሱ ነው:: መድረክ ከኢህአዴግና ከመሰል ፓርቲዎች በተሻለ ለሠላም እንደቆመ ያምናል:: የሰላም ዋና መሰረትም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ

ነው ብሎ ያምናል፡፡ ለዚህም ነው ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ኖሮ ዜጎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለምንም ሥጋት የሚንቀሳቀሱበት ሰፊ የፖለቲካ ምሕዳር እንዲኖር አበክሮ እየጠየቀ ያለው፡፡

በፊርማው ሥነ-ሥርዓት ሂደት ወቅት የኢዴፓ ተወካይ አቶ ልደቱ አያሌውና የቅንጅት ተወካይ አቶ አየለ ጫሚሶ ያሰሙት ንግግርም የኢህአዴግ ተወካይ ያቀረቡትን የሚያስተጋባና የሚያጠናክር ነበር፡፡ በድርድሩ ያልተገኙት ሠላም ፈላጊዎች አለመሆናቸውና እንዲያውም አፈንጋጮች መሆናቸውን ያለምንም ሐፍረት ተናግረዋል፡፡ ሁለቱም ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ባልተናነሰ ሁኔታ በመድረኩ ላይ ያላቸውን ጥላቻ በድጋሚ ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡ ይህ ሁኔታቸው መድረኩ ለመደራደርም ይሁን ላለመደራደር ያለውን መብት የተፃረረ ሲሆን ይህን አጋጣሚ በምርጫው ዋዜማ በመድረኩ ላይ ሊያደርጉት የሚፈልጉትን የማጥላላት ዘመቻ መክፈቻ አድርገውታል፡፡

ኢህአዴግ የሥነ-ምግባሩን ደንብ ለማጽደቅ በርካታ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በተገኙበት ከተፈራረመ ጀምሮ ሠፊና አሠልቺ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ስምምነቱ ከአሁን በፊት ታይቶ የማይታወቅ፤ እጅግ ታሪካዊና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ያልታየ እስከማለትም ደርሷል፡፡ በኛ ግንዛቤ ኢህአዴግና ሦስት ፓርቲዎች ያዘጋጁት የሥነ-ምግባር ደንብ ቀርቶ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚደነግገው ሕገ-መንግሥት እንኳን ላለፉት 17 ዓመታት በገዢው ፓርቲ ሲረገጥ ቆይቷል፡፡ አሁንም እየተረገጠ ነው፡፡ እንደራደር እያልን ያለነው ለይስሙላ ሳይሆን ከሁሉ በፊት እነዚህ በሕገ-መንግሥቱ የሠፈሩት መብቶች ተግባራዊ ሆነው በአገራችን ነፃ፤ ፍትሓዊና ተአማኒ ምርጫ ኖሮ የዴሞክራሲ ምሥረታ ሂደቱ እውን እንዲሆን ነው፡፡ አበይት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በግፍ እየተረገጡ በምርጫ ሥነምግባር ላይ ለተደረሰ ስምመነት አገር አደባላቂ የፕሮፓጋንዳ ከበሮ መደለቅ ሕዝብን ለጊዜው ከማደናገርና ትዝብት ከማትረፍ በስተቀር ሌላ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ለነገሩማ በ97ቱ ምርጫም የሥነ-ምግባር ሰነድ ተፈርሞ ነበር፤ ምርጫውን በፍፃሜው ከታየው ቀውስ አላዳነውም እንጂ፡፡

ከኢህአዴግ የሁለትዮሽ ድርድር ብሎ ነገር የለም በሚል ሰበብ መድረክን ከድርድሩ ማግለሉ በፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ ያላቸውን ተቃዋሚቻችን ማግለል መሆኑን መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በፓርላማ ከፍተኛ መቀመጫ ያላቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላከተተና ይሁንታ ያላገኘ የሥነ-መግባር ደንብ ደግሞ

በዋነኝነት የኢህአዴግ ብቻ መሆኑ ነው:: ይኸም የምርጫ ሥነ-ምግባር ኮድ የገዢው ፓርቲና የተቃዋሚዎች ሰነድ ነው የሚለውን መሠረታዊ መነሻ የሚንድ ነው::

ከፎርማ ሥነ-ሥርዓቱ ማግሥት የታየው ሌላው ክስተት ደግሞ አራቱ ፓርቲዎች በአገሪቱ ያሉት ህጋዊ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጠርተው እነሱ በተስማሙበት የሥነ-ምግባር ደንብ እናወያያችሁ ማለታቸው ነው:: ቦርዱ ቢያንስ በሕግ የተደነገገ ደነብና መመሪያ የማውጣት ሰፊ ሥልጣን ተሰጥቶታል:: በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 110 መሠረት «አዋጁን ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል» ይላል:: ይህ ሥልጣን ለሌላ ፓርቲ ወይም የመንግሥት አካል የተሰጠ አይደለም:: እንዲሁም በአንቀጽ 105 «ቦርዱ የሚመለከታቸውን አካላት በማማከር ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ማከናወን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ተጨማሪ ዝርዝር የምርጫ ደንብ ሊያወጣ ይችላል» ይላል:: እንግዲህ ይህም ቢሆን ገዢውን ፓርቲ ወይንም የተወሰኑ ፓርቲዎችን ማማከር የሚል የለበትም:: «የሚመለከታቸው» የሚለው ፖለቲካ ፓርቲዎች በሚል የሚተረጎም ከሆነም ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፓርቲዎች ተመሳሳይ መብት ያላቸው መሆኑ ታውቆ መካሄድ ይኖርበታል:: ካልሆነ አሁን እያደረገ እንዳለው የገዢውን ፓርቲና ሦስት ተጨማሪ ፓርቲዎችን መርጦ የተቀሩትን ሊያወያይ ወይም ሊያስጠምቅ ሕጉ አይፈቅድለትም:: የነዚህን ፓርቲዎች ሃሳብ ለግብአት መጠቀም ከፈለገም ከአሁን በፊት ሌሎች ፓርቲዎች ተጠይቀው እንዳደረጉት ሁሉ ረቂቆችን ወስዶ መጠቀም ይችላል:: ከዚያ ያለፈ ጣልቃ ገብነት መፍቀድ ከወዲሁ ምርጫው ነፃና ፍትሓዊ እንዳይሆን የሚያደርገው ይሆናል:: የዚህ ሁሉ ትርምስ ዋና ምክንያት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን በአግባቡ ተጠቅሞ መሥራትና ማሠራት በአለመቻሉ ነው::

ብዙ የተነገረለትና በከፍተኛ ሥነ-ሥርዓት የአራት ፓርቲዎች ፊርማ የኖረበት የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 101 እስከ አንቀጽ 105 ባሉት የምርጫ ሥነ-ምግባር መርሆዎችና የምርጫ ቦርዱ ለፓርቲዎች ካሠራጨው የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ብዙ የተለየ ፍሬ ነገር አላገኘንበትም:: እንዲያውም ክልከላዎችንና ግዴታዎችን ያካተተ፣ በሂደቱ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሀቀኛ ተቃዋሚዎችን ያገለለ፣ የምርጫ ቦርድ ከአሁን በፊት ያወጣውንና ለውይይት የተሰራጨውን ደንብ በመተካት በደንብ ላይ ደንብ ለመጨመር ያለመ በመሆኑ በምርጫው ፍትሓዊነትና ነፃነት የሚጨምረው ፋይዳ እምብዛም አይሆንም::

በኢህአዴግና ደጋፊዎቹ የተቀረፀው የሥነ-ምግባር ደንብ የምርጫ ቦርድን ደንብ የማውጣት ሥልጣን ከመንጠቁ በተጨማሪ ደንቡን በመቅረጽ ረገድ መሥራች ናቸው ለተባሉት  አራት ፓርቲዎች በሚቋቋመው ምክር ቤት ልዩና ወሳኝ መብት ያጎናጽፋቸዋል:: ለምሳሌ በአመራሩ ከፍተኛ ኃላፊነት ቦታ መያዝና የፋይናንስ ድልድልን በተመለከተ በነዚህ አራት መሠራች ፓርቲዎች ይወሰናል:: ይህም ኢህአዴግና ልሎች መሰራቾች ወሳኝ ቦታ እንዲኖራቸው የሚያደርግ አካሄድ ነው:: በመሆኑም በምርጫው ሂደት ሁሉም ፓርቲዎች እኩል መብት አላቸው የሚለውን መሠረታዊ መርህን ይፃረራል::

መድረክ ከተቋቋመ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ እየሠራ ነው:: አሁንም ገዥው ፓርቲ በሚያደርስበት ግፍና የማጥላላት ዘመቻ ተሸነፎ ከምርው ሂዴት ራሱን አያገልም:: ከገዥው ፓርቲ የተሻለ አማራጭና ተአማኒነት ስላለው የሚደርስበትን ጫና እየተቋቋመ ለመጪው ምርጫ ራሱን እያዘጋጀም ገዥው ፓርቲ የሚያደርስበትን በደል ይቃወማል:: በዚህ አጋጣሚ ገዥው ፓርቲም እየተከተለ ያለውን አፍራሽ እንቅስቃሴ በማቆም ለመድብለ ፓርቲ እውነተኛ አሠራር  ሁኔታዎችን እንዲያመቻች አበክሮ ይጠይቃል::

በመሆኑም:-

1ኛ/ በአገራችን ነፃ፤ ፍትሓዊና ተአማኒ ምርጫ ተካሂዶ አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ግንባታ፤ ዘላቂ ልማትና በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ሠላም ይኖር ዘንድ መድረክ ያቀረባቸው የድርድር ነጥቦች ላይ ከኢህአዴግ ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ቢካሄድ፤

2ኛ/ ገዢው ፓርቲ በመድረኩ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም በጽ/ቤቶቻቸው እያደረሰ ያለውን መጠነ ሠፊ ወከባና ትንኮሳ በማቆም ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት ያለምንም ቅድመ ሆኔታ ስብሰባዎችና ቅስቀሳዎች ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ ቢመቻች፣

3ኛ/ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ  በርካታ  የፖለቲካ እስረኞች ቢፈቱ፤

4ኛ/ ኢህአዴግ የጀመረውን መድረኩን የማጥላላት ሠፊ ዘመቻ በማቆም ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመቀራረብና አብሮ በመሠራት በአገራችን ሠላምና መረጋጋት የሚሠፍንበትን መንገድ ቢቀይስ:: መጪው ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ ለማድረግ የሚረዳ የመጀመሪያው በር ከፋች ርምጃ ሊሆን ይችላል::

5ኛ/ ስለዚህ ኢህአዴግ የጀመረውን በምርጫ ቦርድና በፓርቲዎች ነፃነት ላይ  ጣልቃ የመግባት እንቅስቃሴ አቁሞ የምርጫ ቦርዱ ነፃ የሚሆንበትንና በአዋጅ የተሰጠውን በአግባቡ የሚጠቀምበትንና የጉዳዩ

ባለቤት የሚሆንበትን እንዲሁም የምርጫ አስፈፃሚ ሠራተኞች ገለልተኛ የሚሆኑበትን መንገድ እንዲከተል ያለንን አስተያየት እንገልፃለን፡፡

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)**
**ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓም**

**አዲስ አበባ**